በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF REVENUES

ቀን ሚያዝያ 2 4 2016
Date
ቁጥር 1.0/246/16
Ref.No

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

ባሉበት

ጉዳዩ፦ የጸደቀ መመሪያ መላክን ይመለከታል፤

የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤትን አሠራርን ለመወሰን የወጣን መመሪያ ቁጥር 171/2013 ተሻሽሎና መመሪያ ቁጥር 183/2016 ሆኖ እንዲጸድቅ ተደርጓል:: በመሆኑም በሁሉም አመራርና ፈጻሚ ታውቆ ተፈጻሚ እንዲደረግ አሳስባለሁ::

ከሠላምታ ጋር

ገብሬ ዘብሬ
የሚኒስትር ጽ/ቤት ተወካይ

ግልባጭ፦

- ለታክስ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለታክስ ስርዓት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ቢሮ

ገቢዎች ሚኒስቴር

Phone: +251 11 662 98 00/ 01/02/03/04/05/06/07/08 Fax: /+251 11 662 98 17
face book page: ministry of revenues. FBP: mor Ethiopia Twitter: erca@twitt
Web site: http//www:erca.gov.et P.o. Box: 2559 Addis Ababa, Ethiopia

የበለፀገች ኢትዮጵያ!

አባሪዎች፦

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

  አዲስ አበባ
- ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

  አዳማ
- ለሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት

  ሀዋሳ
- ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት

  ድሬዳዋ
- ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት

  ጅማ
- ለባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት

  ባህር ዳር
- ለመቐለ ቅ/ጽ/ቤት

  መቐለ
- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት

  ኮምቦልቻ

# የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 171/2013 ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 183/2016

አዲስ አበባ

ሚያዚያ፤2016 ዓ.ም

# የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 171/2013 ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 183/2016

የታክስ ዉሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሰራር መመሪያ ቁጥር 171/2013 (በፍትህ ሚኒስትር መዝገብ ቁጥር 855/2014) ላይ የተወሰኑ ድንጋጌዎችን ግልጽ ማድረግ ስለሚያስፈልግ እና የታክስ አስተዳደሩን የበለጠ የሚያሳልጡ ተጨማሪ ድንጋጌዎችን በመመሪያው ማካተት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ገቢዎች ሚኒስቴር በፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 55(2) በተሰጠዉ ስልጣን መሠረት ይህን የማሻሻያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. አጭር ርዕስ

   ይህ መመሪያ "የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 171/2013 ማሻሻያ መመሪያ ቁጥር 183/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ማሻሻያ

   የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት አሰራርን ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 171/2013 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

   1/ የመመሪያው አንቀጽ 2(6) በሚከተለው ማሻሻያ ተተክቷል፤

   "ቡድን" ማለት ባለሙያዎችን፣ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊን ወይም ሰብሳቢውን እንደሁኔታው የታክስ ዉሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ምክትል ስራ አስኪያጅን የያዘ ስብስብ ነው፡፡"

   2/ በመመሪያው አንቀጽ 2 ላይ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 9 ተካትቷል፡፡

   "ባለሙያ" ማለት የጽ/ቤቱን ኃላፊ እና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ሳይጨምር በመመሪያው አንቀጽ 7 ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (4) ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት የተመደበ ወይም የተቀጠረ የጽ/ቤቱ ሰራተኛ ነው፡፡

   3/ የመመሪያው አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሐ) ተሰርዟል፡፡

4/ በመመሪያው አንቀጽ 4 ላይ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች 4፣5፣6 ፣7 ፣8 እና 9 ተካተዋል፡፡

"4/ የቡድኑ አባል በጽ/ቤቱ የሚቆይበት ጊዜ 4 ዓመት ሲሆን ይህ ጊዜ እንዲራዘም በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ሲቀርብ እንደ አስፈላጊነቱ ሚኒስትሩ የቆይታ ጊዜውን ሊያራዝም ይችላል፡፡

5/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ቢኖርም በሚኒስቴሩ የሰራተኞች መተዳደሪያ ደንብና ይህን ደንብ ለማስፈፀም በወጣ መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ዝውውር በሚኒስተር ሊደረግ ይችላል፡፡

6/ እንደ ሥራው ጥበትና ሥፋት እየታየ እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ቡድን/ኖች በታክስ ውሳኔ አጣሪ ጽ/ቤቶች ሥር ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

7/ ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ የሥራ ክፍል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቡድን/ኖችን በመያዝ በዋናው መስሪያ ቤት ይቋቋማል፡፡

8/ ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ቀርቦ ውሳኔ ያገኘ አቤቱታ ለወደፊት ለህግም ሆነ ለአሰራር ማሻሻያ ግብዓት ይሆን ዘንድ በውሳኔው ላይ የጥራት ምርመራ እየተደረገ ለሚኒስትር ሪፖርት ለማድረግ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቡድን/ኖች በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል የሥራ ክፍል ስር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

9 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተገለጸው ቢኖርም የቡድኑ አባል የቆይታ ጊዜውን ሳይጨርስ በደረጃ እድገት ወይም በሥነ-ምግባር ግድፈት ከጽ/ቤቱ ሊወጣ ይችላል፡፡"

5/ የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2) እና (3) ተሰርዞ እንሚከተለው ተሻሽለዋል፡፡

"1/ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት የሚሰራ ባለሙያ ተፈላጊው የትምህርት ዝግጅት፣ ችሎታና የሥራ ልምድ ማሟላቱ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተረጋግጦ ሲቀርብ በተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ቢሮ በኩል ለሚኒስትር ቀርቦ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡

2/ ተፈላጊውን መስፈርት የሚያሟላ ባለሙያ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ካልተገኘ፣ መስፈርቱን የሚያሟላ ባለሙያ ከዋናው መስሪያ ቤት ወይም ከሌላ ቅ/ጽ/ቤት መስፈርቱን ያሟላ ባለሙያ በተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ቢሮ ተረጋግጦ ሲቀርብ በሚኒስትር ይመደባል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተገለጸው ቢኖርም በሚኒስቴሩ የሰራተኞች አስተዳደር ደንብ መሰረት ተፈላጊውን የትምህርት ዝግጅት፣ችሎታና የሥራ ልምድ የሚያሟላውን ባለሙያ ሚኒስትሩ ሊመድብ ወይም ሊቀጥር ይችላል፡፡"

6/ በመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ "ንዑስ አንቀጽ 4" የሚለው ተሰርዞ "ንዑስ አንቀጽ 5" በሚል ተተክቷል፡፡

7/ የመመሪያው አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፡፡

"2/ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በታክስ ህጉ መሰረት እንዲደርሰው ከተደረገበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በሃያ አንድ ቀናት ውስጥ በውሳኔው ላይ የቅሬታ አቤቱታ ያቀረበ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡"

8/ በመመሪያው አንቀጽ 10 ላይ "ፀሀፊ" የሚለው ተሰርዞ "የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ባለሙያ" በሚል ተተክቷል፡፡

9/ የመመሪያው አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዟል፡፡

10/ በመመሪያው አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 2፤3 እና 4 የነበሩት በአንቀጽ 11 ላይ፤ ንዑስ አንቀጽ (7)፣ (8) እና (9) ሆነው የተካተቱ ሲሆን በዚህ አንቀጽ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 10 ተጨምሯል፡፡

"7/ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ውሳኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ማንኛውም ሰው ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ እንዲቀርብለት ወይም እንዲያስረዳ በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ከማቅረቡ በፊት የሚመለከተውን ሰው ወይም አካል መጠየቅ ይችላል፡፡

8/ ከኦዲት የሥራ ክፍል ወይም ከሌላ የታክስ ውሳኔውን ከሰጠው የሥራ ክፍል የማቅረቢያ ጊዜያቸው ተገልጾ እንዲቀርቡ የሚፈለጉ ማብራሪያዎች ወይም የታክስ አወሳሰን ሪፖርቶች ወይም ለቀረበው ቅሬታ የጽሁፍ መልስ ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት መቅረባቸውን ይከታተላል፣ያረጋግጣል።

9/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 ያልፈፀመ የኦዲት ወይም በሚኒስቴሩ ሌላ የሥራ ክፍል ኃላፊ ወይም ባለሙያ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ በኩል ቅሬታው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተቋማዊ ስጋት ሥራ አመራርና ሥነ-ምግባር የሥራ ክፍል ሲቀርብ ተጠያቂነትን ያስከትላል።

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 የተደነገገውን እና ሌሎችን የመመሪያውን ድንጋጌዎች ላለመፈፀም በቂ ምክንያት ሳይኖር ያልፈፀመ ወይም ያላስፈፀመ የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ባለሙያ በሚኒስቴሩ የሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።"

11/ የመመሪያው አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2) ፣ (3) እና (4) ተሰርዟል።

12/ የመመሪያው አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (6) ተሰርዞ እንሚከተለው ተሻሽሏል።

"6/ ቅሬታ የቀረበበት የታክስ ውሳኔ ሲወሰን ያልታየ ማስረጃ ስለመኖሩ ተገልጾ በታክስ ከፋዩ ቅሬታ ከቀረበ፤

ሀ/ የተገለፀውን ማስረጃ ተገቢነት በተመለከተ ውሳኔውን የሰጠው የታክስ ባለስልጣኑ የሥራ ክፍል እና ቅሬታ አቅራቢው በጋራ እንዲናበቡ ጽ/ቤቱ በጽሁፍ ሊጠይቅ ይችላል።

ለ/ የታክስ ውሳኔውን የሰጠው የታክስ ባለስልጣኑ የሥራ ክፍል እና ቅሬታ አቅራቢው በጋራ መናበብ የተደረሰበትን ውጤት መግለጫ፣የታክስ ውሳኔውን የሰጠው የሥራ ክፍል በጽሁፍ ለጽ/ቤቱ ማቅረብ አለበት።

ሐ/ በጽሁፍ ለጽ/ቤቱ የቀረበው በመናበብ የተደረሰበት ውጤት መግለጫ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያለው ወይም የሌለው ስለመሆኑ በጽ/ቤቱ ሊገልጽ ይገባል።"

13/ ቅሬታው ከታክስ ስሌት ጋር የተገናኘ ከሆነ ታክስ ከፋዩ በታክስ ስሌቱ መሠረት መክፈል ያለበትን እና በቅሬታ ማስታወቂያው ተቃውሞ ያላቀረበበትን ታክስ ሊከፍል ይገባል፡፡

3. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር ተፈርሞ እና በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ እንዲሁም በገቢዎችና በፍትህ ሚኒስቴር ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ፤ሚያዚያ 2016 ዓ.ም

አይናለም ንጉሴ

የገቢዎች ሚኒስቴር ሚኒስትር